| |
|---|
| አንደኛ ዓመት ቁ. ፩<br>1st Year------No.1 |

| |
|---|
| አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፩<br>Addis Abeba 21st December, 1998 |

በክልል 14 መስተዳደር

# አ ዲ ስ ነ ጋ ሪ ጋ ዜ ጣ

# A D D I S N E G A R I G A Z E T A

## REGION 14 ADMINISTRATION

| ያንዱ ዋጋ 0.60 | በክልል 14 ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሳጥን ቁጠር 2445 |
|---|---|---|


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፩ ዓ.ም

የክልል አሰራ አራት መስተዳድር

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ . . . ገጽ ፩


አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፩ ዓ. ም.

### የክልል አሰራ አራት መስተዳድር

### አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የክልል አስራ አራት ክላዊ መስተዳድር በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚያስችሉ የራሱ ሕጎች በክልሉ ምክር ቤት ተመክረው የወጡና የሚወጡ በመሆኑ፤

በክልሉ ምክር ቤት የተለያዩ ሕጎች ኃይል ኑሯቸው ተፈጻሚ የሚሆኑት የሕጉ ተጠቃሚ የሆነው ሕዝብና የክልሉ መስተዳድር የሕግ አወጭ የሕግ ተርጓሚና የሕህግ አስፈጻሚ አካላት በሕዝብ ጋዜጣ በቅድሚያ እንዲያውቁት ሲደረግ ስለሆነ ሕጎቹ የሚወጡበት ኦፊሴል ጋዜጣ ማቋቋመ በማስፍለጉ፤

በክልል አስራ አራት የሽግግር መስተዳድር ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፳፪ መሠረት የሚከተለው ታውጅዋል።

**አንቀጽ ፩**

፩. አጭር ርእስ

ይህ አዋጅ "የክልል አስራ አራት አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ ፪**

፪. መቋቋም

በዚህ አዋጅ "አዲስ ነጋሪት ጋዜጣ" ተብሎ የሚጠራ የክልሉ መስተዳድድር ጋዜጣ ተቋቁሟል።

**አንቀጽ ፫**

**በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚወጡ ጉዳዮች**

፩. በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚወጡ ጉዳዮች ለክልሉ መስተዳድር የተለያዩ አካላት በክልሉ ሕገ መንግስት በተሰጣቸው ሥልጣን መሰረት፣
   ሀ) የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች፣
   ለ) ከፍተኛ የክልሉ ባለስልጣኖቸ ሹመት፣ ሽረት፣ የማዕረግ ስም ሽልማትና ኒሻን፣
   ሐ) ለህዝብ ጥቅም ያላቸው የክልሉ ህዝብ ማወቅ የሚገባቸው ማስታወቂያዎች ናቸው።

፪. ስለሆነም በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚወጡ ሕጎች በክልሉ ሕገ መንግስት ደንብ ለማውጣት ሥልጣን ባላቸው አካሎች ከዚህ በላይ የተገለጹት ጉዳዮዮችን ለሕዝብ ለማስታወቅ የሚወጡ አዋጆች ድንጋጌዎች ደንቦች እና የህግ ክፍል ማስታወቂያዎች ይሆናሉ።

**አንቀጽ ፬**

፫. የአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ቅርጽ (ፎርም)
   ሕጋዊ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሠራ አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚከተለውን ቅርጽ (ፎርም) የሚያሟላ ነው፤

፩. አዲስ ነጋሪ ጋዜጣው ተከታታይ ቁጥሮች በመያዝ የክልሉን መስተዳደር አርማ ያለው ሆኖ የማዕከ

ላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ቅርጽ (ፎርም) ይኖረዋል።

፪. በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ግርጌ የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ማህተም ያረፈበት መሆን አለበት።

**<u>አንቀጽ ፫</u>**

፬. የሕጎች ተፈጻሚነት

በዚህ አዋጅ በተቋቋመ አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚወጡ አዋጆች፣ ድንጋጌዎች ደንቦችና ሌሎች የሕግ ክፍል ማስታወቂያዎች በማንኛውም የክልሉ መስተዳደር አካላት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

***<u>አንቀጽ ፮</u>***

፭. ***<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>***

*ይህ ዓዋጅ በዚህ ዓዋጅ መሠረት በተቋቋመ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።*

*አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም*